
ንስሃ እና ይቅርታ
ትምህርት 10 ለ ግንቦት 29፣ 2018

“በኃጢአታችን
ብንናዘዝ
ኃጢአታችንን ይቅር
ሊለን ከዓመፃም
ሁሉ ሊያነጻን
የታመነና ጻድቅ
ነው።”

(1 ዮሐንስ 1:9)



መጽሐፍ ቅዱስ “ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤” ይላል(ሮሜ 3:23)።


ደግሞም ኃጥያታችንን ልንተው ወይም ልናስወግድ እንደማንችልም ይነግረናል (ኤር 13:23፣ 2:22)።

ነገር ግን እግዚአብሔር ኃጥያታችንን ይቅር ሊለን ፈቃዱ ነው። እግዚአብሔር ይቅር ሊለው የማይችለው እጅግ ታላቅ ወይም እጅግ የከፋ ኃጥያት የለም (ኢሳ 1:18)።

አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ አንድ ነው። እርሱም ንስሃ ነው።







- ንስሃ:
  - ንስሃን ማቆየት
  - እውነተኛ ንስሃ
  - የንስሃ ጥሪ
- ይቅርታ:
  - የይቅርታ ጸጋ
  - የይቅርታ መጎናጸፊያዎች



# ንስሃ



# ንስሃን ማቆየት

"ኢየሱስም መልሶ፡- ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥" (ሉቃስ 10:41)

ኢየሱስ በአልአዛር ቤት ውስጥ ለመዳን አስፈላጊ የሆኑ ዋና ነገሮችን ተናግሮ ነበር። ነገር ግን ማርታ አላደመጠችውም ነበር። ለማዳመጥ ጊዜ አልነበራትም ነበር። ብዙ ስራ ነበረባት! (ሉቃ 10:40-41)።





ይህ አይነቱ ነገር እኛንም ሲያጋጥመን ይስተዋላል። ኃጥያት በሰራን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወደ ንስሃ ሲጠራን ያለንበትን መጥፎ ሁኔታ አስተውለን ይቅርታን እንዳንጠይቅ ሰይጣን በሩጫ፣ በሃሳብ ወይም በሌላ ማዘናጊያ ይከብበናል።






እግዚአብሔር ግን በልጆቹ ተስፋ አይቆርጥም። ጥሪውን አያቋርጥም (ሕዝ 33:11)። በእርሱ ፊት ጽድቃችን እንኳን እንደ መርገም ጨርቅ ነው (ኢሳ 64:6)። ስለዚህ የእኛን ያደፈ ልብስ (ዘካ 3:4) እርሱ በሚሰጠን በኢየሱስ ደም በታጠበው ንጹህ ልብስ ሊለውጥልን ይፈልጋል (ራዕይ 7:14)።



# እውነተኛ ንስሃ

"ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱ ሰብሮናልና፥ እርሱም ይፈውሰናል፤ እርሱ መትቶናል፥ እርሱም ይጠግነናል።" (ሆሴዕ 6:1)



ንስሃ ምንድን ነው? የእውነተኛና የይስሙላ ንስሃ ልዩነት ምንድን ነው? (2ቆሮ 7:10)

አንድ ኃጥያት ወዲያውኑ ያልተፈልገ ውጤትን ሲያስከትል ጸጸት ይሰማናል። የሰራነው ስራ መጨረሻው ጥሩ አለመሆኑ የሚያሳዝን ነው። ከፉ ውጤቶች ባይከተሉ ኖሮ ግን ለድርጊታችን ሃዘን አይሰማንም ነበር። ይህ እውነተኛ ንስሃ አይደለም።



ክፉ ውጤቶች ቢከተሉም ባይከተሉም ኃጥያት መስራታችን በራሱ ካሳዘነንና ይቅር የመባል ጥልቅ ፍላጎትን ከፈጠረብን እውነተኛ ንስሃን አኘተናል ማለት ነው።

መንፈስ ቅዱስ ኃጥያትን ስንሰራ በከባድ የሃዘን ስሜት "ይሰብረናል" እና "ይመታናል"። ምላሻችን እውነተኛ ንስሃ ከሆነ እግዚአብሔር ኃጥያታችንን ይቅር ብሎ ይፈውሰናል (ሆሴ 6:1)።

# የንስሃ ጥሪ

"እንግዲህ ኃጥያታችሁ እንዲደመሰስ ንስሃ ግቡ፤ ከመገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣልችኋል፤" (የሐዋ 3:19 አ.መ.ት)



ኢየሱስ እና መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎታቸውን የጀመሩት "ንስሃ ግቡ" በሚል ተመሳሳይ መልዕክት ነበር (ማቴ 3:1-2፣ 4:17)።

ንስሃ መግባት ለምን ያስፈልጋል? ምክንያቱም ያለ ንስሃ የኃጥያት ይቅርታ ስለማይገኝ ነው (የሐዋ 2:38፣ 3:19)። የዚህ ሂደት እንዴት ነው?



እግዚአብሔር ከመልካምነቱ የተነሳ ወደ ንስሃ ይጠራናል (ሮሜ 2:4)

እኛ ለጥሪው ምላሽ እንሰጣለን

እግዚአብሔር ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስላፈሰሰው ደም ሲል ኃጥያታችንን ይቅር ይለናል (ቆላ 1:13-14)

ለፈጸምነው ስህተት ከልብ እናዝናለን

በእውነት ኃጥያትን ለመተው እንወስናለን



ንስሃና ይቅርታ ሁልጊዜ ወደ መታደስ ሊመራን እንደሚገባና ኃጥያትን መስራት ወደ ሚያስተወን አመለካከት ሊቀይረን እንደሚገባ እዚህ ጋር ማስተዋል አለብን (ዮሐ 5:14)።





# ይቅርታ



# የይቅርታ ጸጋ

“አቤቱ፥ ኃጢአቴ እጅግ ነውና ስለ ስምህ ይቅር በለኝ” (መዝ 25፡11)



እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዲለን የሚያስገድደው አንዳች ነገር የለም። ለዚህም ይቅርታ የተገባን እንድንሆን ማድረግ የምንችለው አንድም ነገር የለም። እግዚአብሔር ይቅርታን የሚሰጠን በጸጋው ከማያልቀው ፍቅሩ ነው። ይቅር የሚለን እርሱ መልካም “መሐሪና ይቅር ባይ . . .፥ ምሕረቱም ለሚጠሩት ሁሉ ብዙ” ስለሆነ ነው (መዝ 86:5፤ ዘጸ 34:6-7)።

የእርሱ ፍቅር በመስቀል ላይ እራሱን እንዲሰጠንና ልንከፍለው የማንችለውን የኃጢያታችንን ዕዳ በሕይወቱ እንዲከፍልልን አድርጎታል (ኤፌ 2:4-5)።





ኃጥያቶቻችንን ወደ መስቀሉ ግርጌ ስናመጣቸው ኢየሱስ ካጎበጠን ሸክማችን ነፃ ያወጣናል (ዕብ 12:1-2)



# የይቅርታ ጸጋ

"አቤቱ፥ ኃጢአቴ እጅግ ነውና ስለ ስምህ ይቅር በለኝ" (መዝ 25:11)



በኃጥያት እና በጸጋ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው ?

## የኃጥያት እና የጸጋ ግንኙነት

**ሮሜ 5:8**
- "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን"
- "ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአል"

**ሮሜ 5:20**
- "ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት"
- "ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ"

**ሮሜ 5:21**
- "ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ"
- "ጸጋ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ ለዘላለም ሕይወት ነገሠ"

**ሮሜ 6:23**
- "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና"
- "የእግዚአብሔር ስጦታ ግን የዘላለም ሕይወት ነው"



# የይቅርታ መጎናጸፊያዎች

“የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው እርሱም ዝም አለ።” (ማቴ 22:12)

የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ደግሞም እያንዳንዱ አባል “እድፈት ወይም መጨማደድ” በሌለበት “ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ” እንዲጎናጸፉ ተሰጥቶአቸዋል (ራዕይ 19:8፣ ኤፌ 5:27)።



ይህ ቀጭን የተልባ እግር “የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ” ተምሳሌት ነው (ራዕይ 19:8ለ)። ነገር ግን ይህ ጽድቅ የራሳቸው ሳይሆን ክርስቶስ የሰጣቸው ነው (ራዕይ 7:14)።





አዳም እና ሔዋን ኃጥያትን በሰሩ ጊዜ እራቁትነታቸውን በራሳቸው ሥራ ለመሸፈን ሞክረው ነበር። እንደዚያም ሆኖ ግን እራቁትነታቸው እየተሰማቸው ነበር (ዘፍ 3:7-10)። እግዚአብሔር የሰጣቸው ልብስ ግን ኃጥያታችንን የሚያስወግደው ፍጹም የሆነው ጽድቁን የሚወክለውን ክርስቶስ ለእኛ የሰጠንን “የሰርግ ልብስ” ነው (ዘፍ 3:21፣መዝ 51:7-10)።



ይህንን ልብስ ሳይለብስ ወደ ሰማይ የሚሄድ ማንም የለም (ማቴ 22:1-14)።

“የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የሚፈልግ ካለ ንስሃ እና ይቅርታን ለማግኘት ከክርስቶስ ሥርየት በስተቀር ምንም ነገር ብቁ ያለመሆኑን እውነት መቀበል አለበት። ኃጥያተኛው በዚህ እርግጠኛ በመሆን ለእርሱ ከተሰራለት ሥራ ጋር በመስማማት ጥረት ማድረግና በማይደክም ልመና የሚያድሰው የእግዚአብሔር ኃይል ወደ ነፍሱ ውስጥ እንዲመጣ የጸጋ ዙፋኑን መማጸን አለበት። ክርስቶስ ከሚጸጸቱት በቀር ማንንም ይቅር አይልም፤ ነገር ግን አስቀድሞ ይቅር የሚላቸውን እንዲጸጸቱ ያደርጋቸዋል። የመጣው እርዳታ የተጠሟላ ይሆናል፤ እናም የክርስቶስ ዘላለማዊ ጽድቅ ለእያንዳንዱ የሚያምን ነፍስ ይበረከታል። በሰማያዊ መጋቢያ የተሸመነው ውዱና ነቁጠ ቢስ የሆነው ልብስ ንስሃ ለሚገባውና አማኝ ለሆነው ኃጥያተኛ ቀርቧል።”

EGW (Selected Messages, vol. 1, p. 393)